በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ለሚፈልግ ሀገር ወዳድ ሁሉ፤

ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፤

ሴኔተር ባራክ ኦባማ፣ “የአሜሪካ አስተዳደር ሁል ጊዜም ሕዝብን የሚጨቁኑ ዲክታተሮችን ይደግፋል” ብለው ሲናገሩ ተሰምተዋል። የሚቀጥለውን አስተዳደር ለመምራት ዕድል ካላቸው ተወዳዳሪ አፍ እነዚህን ቃላት መስማት ለዓለም ጭቁን ሕዝብ የተስፋ ጮራ ይፈነጥቃል። ምናልባት የኢትዮጵያ ዋይታ ሰማያዊና ምድራዊ ጆሮ የሚያገኝበት ጊዜ መጥቶ ይሆናል። ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው ሁሉ ሌላውን የሚሉት “ጠላታችንን አትደግፉብን” ነው እንጂ፣ ነፃ አውጡን ብለው አያውቁም። ዛሬም እኛ ልጆቻቸው የምንለው አባቶቻችን ይሉት የነበረውን ነው፤ ለነፃነታች የመታገሉን ክብር ለማንም አናጋራም። ከአሜሪካም ሆነ ከሌሎች አገሮች የምንጠብቀው ሴኔተር ኦባማ እንደሚያምኑበት ዲሞክራት አገሮች የዲክታተሮች አለኝታና መከታ እንዳይሆኑ ነው።

ለነፃነታችን የመታገሉን ክብር ለማንም ሳናጋራ እንደ አባቶቻችን እኛው እንፈጽመዋለን ካልን፣ ጨቋኙን ፋታ ሳንሰጠው ማዋከብ ይኖርብናል። በጭቆና የምንማቅቅ መሆናችንን ለዓለም የምናሳውቀውና የምንታመነውም በተቃውሞ ስንሟሟት ነው። እንዲህ ያለ ተጋድሎ የማያይ ጎብኚና ሰላይ ላይ ላዩን ብቻ አይቶ ውስጥ ውስጡን የሚካሄደውን ጭቆና ሳያይ ይቀራል፤ ዟዙሮ አይቶ፣ “በሀገሪቱ ላይ ሰላም ሰፍኗል፤ መንገድ በያለበት ይቀደዳል” ብሎ ይሄዳል እንጂ የምትቀደደው ራሷ ኢትዮጵያ መሆኗን ሊገነዘብ አይችልም። በሀገር ውስጥ ያሉት ታጋዮች ለሰላማዊው ትግል ዘዴ እያወጡለት እንደሆነ እገምታለሁ። መቸም ሰላማዊ ትግል ማለት ለጨቋኙ ሰላምታ መስጠት ወይም ከቤተ መንግሥት እየተመላለሱ ደጅ መጥናት ሳይሆን፣ በየጎራው ላይ “አሻፈረኝ፣ አልዳኝም” ባይ ሆኖ መገኘት ወይም በእንግሊዝኛ አነጋገር “Passive resistance” or “Civil disobedience” መሆኑን የተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ እንደሚያውቁት አልጠራጠርም።

ይኸ በእነሱ በኩል ስለሚደረገው ነው። በእኛ በኩልስ? በሀገር ጉዳይ ላይ በመሠረቱ “እኛ” እና “እነሱ” የሚባል ነገር የለም። ወደዚያው እየሄድንም ተመልሰን እየመጣንም ትግሉን በአንድነት ማፋፋም ይኖርብናል። ስንሄድ አብረናቸው እንዋደቃለን፤ ስንመለስ ከኪሳችን ገብቶ ይዞ የሚወጣ እጃችንን እንዘረጋላቸዋለን። ትግሉን በዚህ ሁኔታ ለማካሄድ ከመቸውም የበለጠ የሚያስፈልገው አሁን ነው። በቅርቡ ምርጫ እንደሚካሄድ ሁላችሁም ታውቁ ይመስለኛል። “እንግዴህ ወዲህ የምርጫውን ነገር አታንሣብን” ብላችሁ ፊታችሁን ከምታዞሩብኝ በፊት ባይሆን ንግግሬን አስጨርሱኝ። እኔም የምርጫ ወሬ በሰማሁ ቍጥር፣ እንደብዙዎቻችሁ “የምን ውሐ ቅዳ፤ ውሐ መልስ ነው! እንግሊዝኛ ተናጋሪዎችም አልፎ አልፎ የኛ ብጤ ብልሆች ስላሉዋቸው፣ Fool me once; shame on you. Fool me twice; shame on me ይላሉ” ስል ቆይቻለሁ፤ ጽፌያለሁም። ሐሳቤን የለወጥሁት በሁለት ምክንያት ነው፤

አንደኛ፣ የተቃዋሚ ቡድኖች ባለፈው ምርጫ ባይሳተፉ ኖሮ፣ አቶ መለስ ዜናዊና ካድሬዎቹ የበግ ቆዳ የለበሱ ተኵላዎች፣ የዲሞክራሲ ጃኖ የተጎናጸፉ ዲክተተሮች መሆናቸው ሳይታወቅባቸው ተኮፍሰው ይኖሩ ነበር። በምርጫው ምክንያት አሁን ዓለም ዐውቋቸዋል። የአውሮፓ ታዛቢዎች መስክረዋል፤ የፕሬዚዴንት ካርተር ቡድን ያወጣው መግለጫ ቡድኑን መልሶ ማሳፈሩን ውስጥ ዐዋቂዎች ደርሰውበታል። ይኼ በዋጋ የማይተመን ውጤት ነው። የአለፈውን ምርጫ ውጤት ዋጋውን ማሳጣት ፖለቲካ አለማወቅ ነው።

ሁለተኛ፣ “በዓምና በሬ አይታረስም” እንደሚባለው፣ በጭቆና ያለን መሆናችንን ጨቋኝ ዲክታተሮችን ለሚደግፉ መንግሥታት ለማስረዳት ያለፈውን የምርጫ ውጤትና ወያኔዎች

ያደረጉትን ብልግና ማሳየት ብቻ አይበቃም። ተጨማሪ ትኩስ ማስረጃ መያዝ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ የሚቀጥለውን ምርጫ ያለፈውን ምርጫ ያህል በገንዘብ እንድትደግፉት አጥብቄ ላሳስባችሁ። ተቃዋሚዎች ከምርጫው ገብተው በገንዘብ ችግር ምክንያት ወያኔ ከአሸነፋቸው የነፃነት ዕድል ተመልሶ የሚመጣበት መንገድ አይታየኝም።

ላስታውሳችሁ የምፈልገው "እናዋጣ" እንጂ "አዋጡ" ብቻ አላልኩም፤ በበኩሌ የማዋጣው ሠርቼ ከማተርፈው ሳይሆን ከጡረታዬ ማንም ሳይሰማ እያሾለኩ ነው። "ማን ከማን ያንሳል" ብላችሁ እንደምትፎክሩና ቃላችሁን እንደምታከብሩ ኢትዮጵያ የምትተማመንባችሁን ያህል እተማመንባችኋለሁ።

ጤና ይስጥልኝ።

EthioLion.Com